# ዴሞክራሲና የዘውግ ብሔርተኝነት

በናትናኤል ፈለቀ

በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ 1983 ዓ.ም በኋላ የሀገሪቱን ስልጣን የያዘው ሕወኃት/ኢሕአዴግ መራሹ አገዛዝ ሀገሪቱን መልሶ ለማ ዋቀር ትክክል ብሎያሰበውን በዋነኝነት ቋንቋን ማዕከል ያደረገ የዘውግ ፌደራል ስርዓት ሲገነባ ቆይቷል፡፡ ይህም በቅርብ ጊዜ የ ሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ የዘውግ ማንነት ተኮርውይቶች ጎልተው አደባባይ እንዲወጡ ዕድል ፈጥሯል፡፡ የሀገሪቱን የፖለቲካ ልሂቃን ውይይት መድረክ የተቆጣጠረው የዘውግ ማንነት ተኮር(ብሔርተኝነት) አጀንዳ ልሂቃኑ በሚያሳዩት የፅንፈኝነት ባህሪ ከጊዜ ወ ደ ጊዜ እየተካረረ መጥቷል፡፡ በዚህም የተነሳ አሁን ስልጣን ላይ ያለው አገዛዝአምባገነናዊ ቢሆንም በለውጥ ምክንያት ከስልጣን ቢወገድ በሚፈጠረው ክፍተት (Vacuum) ጊዜ ውስጥ የዘውግ ማንነት ተኮር የእርስ በርስ ግጭትሊነሳ ይችላል ብሎ በመፍ ራት አምባገነናዊ ባህሪውን ይዞም ቢሆን ሕወኃት/ኢሕአዴግ መራሹ አገዛዝ “ይቆይልን” የሚል አስተያየት ያላቸው ሰዎችጥቂት አይደሉም፡፡ ከዚህ ከፍ ሲል ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት አሁን ሀገሪቱ ውስጥ አለ ብለው የሚያምኑትን የዘውግ ተኮር ግጭቶ ች ስጋትለመቆጣጠር “ልፍስፍስ ስለሆነ አምባገነናዊ ስርዓት አሁን ላለንበት ተጨባጭ የማኅበራዊ-ፖለቲካ ሁኔታ ተመራጭ ነ ው” የሚሉ ሃሳቦችምይሰማሉ፡፡

በርግጥ ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት አስተያየቶች የሚሰነዝሩ ሰዎች ሀገሪቱ እስከመቼ በአምባገነናዊ ስርዓት ውስጥ ብትቆይ እንደ ሚሻልና ምን ሲከሰትወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሽግግር ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ግልፅ የሆነ የመፍትሄ
ሀሳብ አብረው ሲሰነዝሩ አይሰማም፡፡ አንድ ነገር ግን ግልፅ ነው፡፡ሀገሪቱን ለአምባገነናዊ ስርዓት ለተራዘመ ጊዜ መተው መዘዙ ብዙ ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቶች የዘውግ ማንነት ተኮር የራስን ዕድልበራስ ለመወሰን የሚነሱ ጥያቄዎችን የሀገ ሪቱን ሉዓላዊ ግዛት አደጋ ውስጥ በማይከት ሁኔታ ማስተናገድ እንደሚችሉ በማሳየት ሀገሪቱ አሁን ባለችበትተጨባጭ ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንደሚያስፈልጋት ይሞግታል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ስለተፈጠረ ብቻ በዘውግ ብሔርተኝነት ምክንያ ትየሚፈጠር የግጭቶች ስጋት ተኖ ይጠፋል ማለት አይቻልም፡፡ ጽሑፉ
ለማስረዳት የሚሞክረው ዴሞክራሲያዊ መንግስት (ስርዓት) በኢትዮጵያ ውስጥሲገነባ ችግሩ አሁን ካለበት ደረጃ የበለጠ አስጊ እንደማይሆን እና ከኢትዮጵያ በፊት ተመሳሳይ ስጋት የነበረባቸው ሀገራት ዴሞክራሲን ተጠቅመውችግሩን እንዴት እንዳለፉት ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዴትና በማን ይመጣል የሚሉት ጥያቄዎች
በዘውግ ብሔርተኝነት ጥያቄመልስ ማግኘት ውስጥ ግብዓቶች ቢሆኑም ከዚህ ጽሑፍ ወሰን (Scope) በላይ ናቸው፡፡

የዘውግ ማንነት ተኮር የፌደራል ስርዓት ለምን ኢትዮጵያን ይበታትናል**?**

የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኦዴግ) የሚባል ድርጅት በአዲስ መልክ አደራጅተው ወደ ኢትዮጵያ ፖለቲካ የተመለሱት ሌን ጮ ለታ በጻፉት አንድጽሑፍ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ወደስልጣን ሲመጣ የነበረው የሀገሪቱ የፖለቲ ካ ሁኔታ (setting) የዘውግ ማንነት መሰረትያደረገ የፌደራል ስርዓትን እንዲከተል ከታሪክ የተረከበው የውዴታ ግዴታ እንደ ነበር እና ብቸኛ ሀገሪቱን ከመበታተን ለማዳን የሚችል ስርዓትእንደነበር አስረድተዋል፡፡ እንደሌንጮ ትንተና ከሆነ የዘውግ ማን ነት ጉዳይ ገዢ ሕዝብን የማደራጃ (mobilizing) ሀሳብ አድርገው የፈጠሩትበዘውግ ማንነታችን ምክንያት ጭቆና ደርሶብና ል ብለው የዘውግ ማንነት ተኮር ድርጅቶችን የመሠረቱ ቡድኖች ሳይሆኑ ከዛ በፊት ዘውግ ተኮር ጭቆናንየፈፀሙ ሀገሪቷን ይገ ዙ የነበሩ ቡድኖች ናቸው በማለት የዘውግ ማንነት ተኮር ንቅናቄዎችን ቀድሞ ለተፈጠረ ችግር ምላሽ ብቻ እንደሆኑ ያስቀምጣ ሉ፡፡

ሌንጮ በጽሑፋቸው የፌደራል ስርዓቶች በተፈጥሯቸው የአገር ግዛት አንድነትን ለማስጠበቅ ጥንካሬ እንደሚያንሳቸው፣ የፌደ ራል ስርዓቱ የተዋቀረውደግሞ የዘውግ ማንነትን (ቋንቋን) መሠረት አድርጎ ከሆነ የበለጠ ደካማ እንደሚያደርገው አትተዋል፡፡ የሌንጮን ሃሳብ የሚያጠናክር ተሞክሮለመጥቀስም የዓለም ግዙፏ ዲሞክራሲ ህንድ ከታላቋ ብሪታኒያ ቀኝ ግዛት ተላቃ ከፓኪ ስታን ጋር ፍቺ ከፈጸመች በኋላ ሃገሪቷን በጠቅላይ ሚኒስትርነትያስተዳድሩ የነበሩትጆዋሃርላል ኔህሩ “የገንጣይነት ስሜትን ያበ ረታታል እና ሀገሪቷን ወደ በለጠ መከፋፈል ያመራል” በሚል ምክንያት
የሕንድፌደራል ስርዓትን ቋንቋን መሠረት አድርጎ መልሶ ለማዋቀር ይነሱ የነበሩ ምክረ ሃሳቦችን ለመቀበል ፍላጎት እንዳልነበላራቸው አቱል ኮህሊ የተባሉየሕንድ ማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪ “Can Democracies Accommod-ate Ethinic Nationalism? Rise and Decline of Self-determination Movements in

India" በሚልርዕስ ባስነበቡት የጥናት ጽሑፍ ውስጥ ጠቅሰዋል፡፡ ኔህሩ የኋላ ኋላ ግን የታሚል ቋንቋተናጋተናጋሪዎች የራሳቸው ፌደራል ግዛት (Tamil Nadu) እንዲኖራቸው ያነሱትን ጥያቄ ተቀብለው የታሚል ቋንቋ ተናጋሪዎች ግዛት እንዲመሠረትአድርገዋል፡፡ የሰጉት የመበታተን አደጋ ግን አልተከሰተም፡፡

አዘጋጅ Zone 9